# የድርድር ሽያጭ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንጋ ዲስትሪክት ስምና አድራሻቸው ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተዘረዘሩት ተበዳሪዎች ለሰጠው ብድር አመላለስ በመያዣነት የያዘውን የመያዣ ንብረቶች ባሉበት ሁኔታ በድርድር አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው/የመያዣ ሰጪው ስም | ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻ | የሚሸጠው ንብረት አይነት | ጠቅላላ የመሬት ስፋት መጠን (ሄክታር) | የለማው የመሬት መጠን (ሄክታር) | የጨረታ ሽያጭ መነሻ ዋጋ(ብር) | የድርድር ሽያጩ የሚካሄድበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢተፋ መኮንን ሃፋ | በጋምቤላ ክልል፤ አኝዋ ዞን፤ ዲማወረዳ፤ አኩላ ቀበሌ | ግንባታ፡ የለማ መሬት እና አይሱዙ ተሽከርካሪ | 1500 | 495.37 | 17,783,591.26 | መጋቢት 25 ቀን 2018 ዓ.ም ከ4፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ተጫራቾች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 1/4ኛ (አንድ አራተኛ) በባንክ ክፍያ ማዘዣ / CPO/ ብቻ በማስያዝ የድርድር ሽያጭ ጨረታ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ማመልከቻቸው ላይ ለመያዣ ንብረቱ የሚያቀርቡትን ዋጋ እና ለመያዣ ንብረቱ የሚከፍሉትን የቅድሚያ ክፍያ መጠን በግልፅ በመፃፍ መጋቢት 24 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 (ሰዓት) በፊት በቦንጋ ዲስትሪክት ጽ/ቤት ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ የድርድር ሽያጭ ሳጥን ውስጥ በማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
3. አሸናፊ የሆነው ተጫራቾች ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ/በ15 በአስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ካልከፈሉ ያስያዙት ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ሆኖ የድርድር ሽያጩ ይሰረዛል፡፡ በተጨማሪ ንብረቱ በድጋሚ ለድርድር ሽያጭ ሲቀርብ በሚታየው የዋጋ ልዩነት ይጠየቃል፡፡
4. ሽያጩ የከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በቦንጋ ዲስትሪክት ጽ/ቤት ሲከፈት ተጫራቾች /ተደራዳሪዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በቦታው በመገኘት ሂደቱን መከታተል ይችላሉ፡፡
5. አሸናፊው ተጫራች (ተደራዳሪ) ያስያዘው ገንዘብ ከግዥው ዋጋ ጋር የሚታሰብ ሲሆን ለተሸነፉት ያስያዙት ገንዘብ ይመለሳል፡፡
6. ገዥው ንብረቱን በገዛበት ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ጨምሮ ሌሎች ገዢ እንዲከፍላቸው በሕግ የተወሰነ ታክስና ግብሮችን፣ የስም ማዛወሪያ ክፍያን ጨምሮ ገዢው/የጨረታ አሸናፊው ይከፍላል፡፡
7. የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች እና የእርሻ መሣሪያዎች ጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ከሆኑ ገዥው የቀረጥ ነጻ መብት ሊኖረው አሊያም በመንግስት የሚፈለውን ቀረጥ መክፈል ይገደዳል።
8. ባንኩ ለድርድር ሽያጭ የቀረበውን የመያዣ ንብረት የሚሸጠው ከተቻለ ሙሉ ለሙሉ በጥሬ ገንዘብ ወይም አሸናፊው በባንኩ የብድር ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር መሰረት አስፈላጊውን መስፈርቶች ካሟላና የፕሮጀክቱን ሥራ የሚያስቀጥል ከሆነ ንብረቱን በከፊል ብድር ለመግዛት መጠየቅ ይችላል፡፡
9. ዝርዝርና ተጨማሪ መረጃን በተመለከተ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦንጋ ዲስትሪክት በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 047331 20-46 ወይም 047-331- 23 11 ደውሎ ማግኘት ይቻላል፤፤ ንብረቶቹን መጎብኘት የሚፈልጉ ካሉ ከቦንጋ ዲስትሪክት ጋር አስቀድሞ ቀጠሮ በመያዝ መመልከት ይቻላል፡፡
10. ባንኩ የተሻለ መንገድ ካገኘ የድርድር ሽያጩን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ቦንጋ ዲስትሪክት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**

DEVELOPMENT BANK OF ETHIOPIA